# ETHIOPIAN CIVIL SERVICE UNIVERSITY

Quarterly Magazine

July- September 2024

***Committed to Excellence in the Public Sector!***




የትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲን ጎበኙ



2016 የበጀት ዓመት የላቀ ዉጤት ላመጡ የስራ ክፍሎች ሽልማት ተሰጠ



33ኛው ሀገር አቀፍ የትምህርት ጉባኤ በኢሲሰዩ ተካሄደ



ECSU Signed MoU with School of Planning and Architecture



የኢሲሰዩ ያስገነባቸውን የንግድ ሱቆች ለተጠቃሚዎች አስተላለፈ

## ራዕይ

ፐብሊክ ሴክተሩን ከመገንባት አኳያ በ2022 በዘርፉ ከተሰማሩት ተቋማት መካከል የላቀ ፣ በቴክኖሎጂ የዘመነና ተወዳዳሪ የልቀት መገንቢያ ተቋም መሆን

## ተልዕኮ

ፐብሊክ ሴክተሩ ውጤታማ የህዝብ አገልጋይ ሆኖ እንዲሰራ አቅሙን በስፔሻላይዝድ ትምህርት ፣ በስልጠና ፣ በማማከር ፣ በጥናትና ምርምር እና በማህበረሰብ አገልግሎቶች በተገቢነት መገንባት

## እሴቶች

ተገልጋይ ተኮር
ልቆ መገኘት
ትብብር መፍጠር
ሁሌም መማር
ፈጠራን ማበረታታት
ዘለቄታዊ ውጤታማነት
ብዝሀነትን መቀበል
ትኩረት ልዩ ድጋፍ ለሚሹ

# Table of Contents


የትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲን ጎበኙ........................................................1

በኢሲሰዩ ሲሰጥ የቆየው የ2016 ዓ/ም የ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ መልቀቂያ ፈተና ተጠናቀቀ..................................1

2016 የበጀት ዓመት የላቀ ዉጤት ላመጡ የስራ ክፍሎች ሽልማት ተሰጠ ........................................................2

ኢሲሰዩ ካውንስል የ2016 ዓመታዊ የስራ ክንውን ግምገማ አካሄደ............................................................. 3

33ኛው ሀገር አቀፍ የትምህርት ጉባኤ በኢሲሰዩ ተካሄደ..........................................................................5

በኢሲሰዩ የችግኝ ተከላ መርሐ- ግብር ተካሄደ...................................................................................6

የኢሲሰዩ ያስገነባቸውን የንግድ ሱቆች ለተጠቃሚዎች አስተላለፈ............................................................................7

ECSU Signed MoU with School of Planning and Architecture......................................................... 8

## የትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲን ጎበኙ

የኢፌዴሪ የትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ፕ/ር ብርሀኑ ነጋ እና የሀገር አቀፍ ትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ዶ/ር እሸቱ ከበደ ሀምሌ 9 ቀን 2016 ዓ.ም በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ በመገኘት በዩኒቨርሲቲው በመሰጠት ላይ የሚገኘውን የ12ኛ ክፍል ሀገርአቀፍ ብሄራዊ ፈተና እና አጠቃላይ የፈተናውን ሂደት በተመለከተ ጉብኝት አድርገዋል።



የኢሲሰዩፕሬዚዳንት ፕሮፌሰር ፍቅሬ ደሳለኝ ለሚኒስትሩ አጠቃላይ ሂደቱን በተመለከተ ገለፃ ያደረጉላቸዉ ሲሆን የመጀመሪያ ዙር የማህበረሰብ ሳይንስ ተፈታኞች ያለምንም እንከን ፈተናቸዉን እንዳጠናቀቁ በመግለጽ የሁለተኛ ዙር የፈተና ሂደት በጥሩ ሁኔታ እየተካሄደ መሆኑን እና ለፈተናው አስፈላጊ ግብአት መሟላቱን ጠቁመው፣ በበይነ መረብ አማካኝነት ፈተናውን ለሚወስዱ ተማሪዎችም በቂ ኮምፒዩተሮች እና ፈጣን የኢንተርኔት አገልግሎት እንዳለ ገልፀውላቸዋል።በማጠቃለያም ላይ ክቡር ሚኒስትሩ አረንጓዴአሻራቸዉንበዩኒቨርስዉዋናግቢችግኝበመትከል አኑረዋል፡፡



በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ በ2016 ዓ.ም እየተሰጠ ባለዉ የ12ኛ ክፍል ሀገርአቀፍ ብሄራዊ ፈተና ለመዉሰድ ለተመደቡ የተፈጥሮ ሳይንስ ተማሪዎች ገለጻ (orientation) ሐምሌ 08 ቀን 2016 ዓ.ም የተሰጠ ሲሆን በተያዘው ሀገራዊ ፕሮግራም መሰረትም በ 09/11/2016 ዓ.ም ፈተናውን እንዲጀምሩ ተደርጓል፡፡

## በኢሲሰዩ ሲሰጥ የቆየው የ2016 ዓ/ም የ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ መልቀቂያ ፈተና ተጠናቀቀ

በኢትዮጵያሲቪልሰርቪስዩኒቨርሲቲከሐምሌ3/11/2016 - 5/11/2016 ዓ.ም ድረስ ሲሰጥ የቆየው የ2016 ዓ.ም የመጀመሪያው ዙር የ12ኛ ክፍል የማህበራዊ ሳይንስ ሀገር አቀፍ መልቀቂያ ፈተና ያለምንም እንከን ሙሉ በሙሉ ሠላማዊ በሆነ መንገድ ተጠናቋል።



የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ፕ/ር ፍቅሬ ደሳለኝ ባስተላለፉት መልዕክት የማህበራዊ ሳይንስ ዘርፍ የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና በተሳካ ሁኔታ ተጀምሮ በሰላም የተጠናቀቀ መሆኑን በመጥቀስ ፈተናዉ በተሳካ ሁኔታ እንዲጠናቀቅ አስተዋጽኦ ላደረጉ የዩንቨርሲቲዉ ከፍተኛ አመራሮች ፣ የፈተና አስፈፃሚ ግብረ-ሀይል አባላት፣ የጣቢያ ኃላፊዎች፣ ሱፐርቫይዘሮች፣ ፈታኞች፣ የፀጥታ አካላት፣ በተመሳሳይ ለሌሎች አገልግሎት ሰጪ አካላት ምስጋና አቅረበዋል፡ ፡ ይህን ሀላፊነታቸዉንም በተቀናጀ መልኩ በቀጣይ ጊዜ ለሚሰጠዉ የተፈጥሮ ሳይንስ ሀገር አቀፍ መልቀቂያ ፈተና ፍፁም ሰላማዊና ስኬታማ በሆነ መልኩ እንዲጠናቀቀ የየራሳቸዉን ድርሻ እንዲወጡ አሳስበዋል።

በተያያዘ ዜና ከማክሰኞ ሐምሌ 09/2016 ዓ.ም ጀምሮ ለተፈጥሮ ሳይንስ ተማሪዎች በወረቀት እና በኦንላይን በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ሲሰጥ የቆየው ሀገር አቀፍ ፈተና ፍፁም ሠላማዊ በሆነ መንገድ ተጠናቋል ። የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ፕ/ር ፍቅሬ ደሳለኝ ባስተላለፉት መልዕክት የተፈጥሮ ሳይንስ ዘርፍ የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና በተሳካ ሁኔታ ተጀምሮ በሰላም የተጠናቀቀ መሆኑን በመጥቀስ ፈተናዉ በተሳካ ሁኔታ እንዲጠናቀቅ አስተዋጽኦ ላደረጉ የዩንቨርሲቲዉ የፈተና አስፈፃሚ ግብረ-ሀይል አባላት፣ የጣቢያ ኃላፊዎች፣ ሱፐርቫይዘሮች፣ ፈታኞች፣ የፀጥታ አካላት፣ በተመሳሳይ ለሌሎች አገልግሎት ሰጪ አካላት ምስጋና አቅረበዋል፡ ፡ለተፈታኝ ተማሪዎች መልካም ዉጤት ተመኝተዋል።

# 2016 የበጀት ዓመት የላቀ ዉጤት ላመጡ የስራ ክፍሎች ሽልማት ተሰጠ

በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ በ2016 የበጀት አመት የላቀ ዉጤት ላመጡ የስራ ክፍሎች የእዉቅና እና ሽልማት ፕሮግራም ተደረገ። ሐምሌ 14 ቀን 2016 ዓ.ም በተካሄደዉ ዓመታዊ የሰራተኞች ቀን ላይ በበጀት አመቱ በስራቸዉ ያሉ ሰራተኞችን በመምራት እና ጥሩ የስራ መንፈስ በመፍጠር ዉጤታማ የሆኑ ሶስት የስራ ክፍሎች የዋንጫ እና የገንዘብ ሽልማት ተበረከተላቸዉ።



የዩኒቨርሲቲዉ ፕሬዚዳንት ፕ/ር ፍቅሬ ደሳለኝ በፕሮግራሙ መክፈቻ ላይ እንዳሉት ይህ ሽልማት ባለፉት ግዚያት የተቋረጠ ቢሆንም በዘንድሮ በጀት ዓመት ማናጅመንቱ በወሰነዉ ዉሳኔ እና ባስቀመጠዉ አቅጣጫ መሰረት ተጀምሯል ብለዋል፡፡ሁሌም እንደመርህ የምንለዉ ዩኒቨርስቲያችን ሲያድግና ሲለወጥ የመንግስት ተቋማትና ሰራተኞች የተሻለና ጥራት ያለዉን አገልግሎት ያገኛሉ፤ በተጨማሪም ሰራተኞች




ያድጋሉ፣ይለወጣሉበሰሩትልክተጠቃሚምይሆናሉብለዋል። የዚህ የእዉቅና እና ሽልማት ዋንኛ ዓላማ በሰራተኞች እና ስራ ክፍሎች መካከል የዉድድር መንፈስ በመፍጠር ለተሻለ ስራ እንዲተጉማድረግሲሆንበተጨማሪምበዚህሂደትዉጤታማ ለሆኑ ክፍሎች እዉቅና እና ማበረታቻ መስጠት ነዉ ብለዋል፡፡በዘንድሮ አመት ሶስት የስራ ክፍሎች ለአፈጻጸማቸዉ እዉቅና የተሰጠ ሲሆን በሚቀጥለዉ በጀት ዓመት ደገሞ ቁጥሩን በመጨመር በሌሎች ዘረፎች ጭምር እንደሚካሄድ ገልጸዋል። ለሲቪል ሰርቪሱ የምንሰጠዉ አገልግሎት መሻሻል እንደተጠበቀ ሆኖ የዩኒቨርስቲያችንን የዉስጥ አቅም በብቁ እና በቂ የሰዉ ኃይል በማሳደጋችን ፣ ለመማር ማስተማሩ አስፈላጊ የሆኑ መሰረተ ልማት በማስፋፋታችን፤ ሌሎች መስፈርቶች ጭምር በማሟላታችን የምርምር ዩኒቨርስቲ መዋቅር ማግኘት ችለናል ብለዋል። አሁንም ከዚህ በበለጠ ዩኒቨርስቲያችንን ለማሳደግ በተሰማራንበት የስራ ክፍልና የስራ ድርሻ በተነሳሽነት መንፈስ ጠንክረን መስራት ይጠበቅብናል ሲሉ መልዕክታቸዉን አስተላልፈዋል፡፡በመጨረሻም ለዩኒቨርስቲዉ ዕቅድ ክንዉን መሳካት የበኩላቸዉን ኃላፊነት ለተወጡ አመራሮች፣የአካዳሚክና የአስተዳደር ሰራተኞች ምስጋና አቅርበዋል። በማጠቃላያዉም ላይ በ2016 ዓ.ም በአስተዳደር እና ልማት ዘርፍ የፋይናንስ ሥራ አስፈጻሚ፣የምህንድስና እና ጥገና አገልግሎት ሥራ አስፈጻሚ እና የስልጠናና ፋሲሊቲእና መስተንግዶ አገልግሎት ስራ አስፈጻሚ በክፍል ደረጃ የእዉቅና እና የዋንጫ ሽልማት ፣ ለስራ አስፈጻሚዎቹ የአስር ሺ ብር ሽልማት ተበርክቶላቸዋል፡



# ኢሲሰዩ ካውንስል የ2016 ዓመታዊ የስራ ክንውን ግምገማ አካሄደ

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ካውንስል የዩኒቨርሲቲውን የ2016 ዓ.ም በጀት ዓመት ዓመታዊ የመደበኛ እና የሪፎርም ስራዎች አፈጻጸም ግምገማ ሐምሌ 16 ቀን 2016 ዓ.ም በህዳሴ አዳራሽ አካሄደ።

በግምገማ መድረኩ መክፈቻ ላይ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚደንት ፕ/ር ፍቅሬ ደሳለኝ ባደረጉት የመክፈቻ ንግግር የግምገማ መድረኩ የበጀት ዓመቱ ማጠቃለያ እንደመሆኑ መጠን የዩኒቨርሲቲውን የዓመቱን ሙሉ ገጽታ የሚያሳይ የግምገማ መድረክ እንደሚሆን ለካውንስሉ ገልጸዋል። በማስከተልም ቀደም ሲል በመንግስት በተፈቀደው በጀት ላይ 346 ሚሊዮን ብር ተጨማሪ በጀት ተገኝቶ በዩኒቨርሲቲው ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በሚባል ደረጃ ከፍተኛ በጀት ከመንግስት የተመደበበት፤ አጠቃላይ በጀቱም 837 ሚሊዮን ብር የደረሰበትና ይህንንም በጀት በተሳካ ሁኔታ ለመማር ማስተማር፣ የምርምር፣ የማማከር ፣ የስልጠና እና ለአስተዳደር ስራዎች ጥቅም ላይ የዋለበት ዓመት መሆኑን ገልጸዋል። ከሪፎርም ዕቅድ አንጻርም ዩኒቨረሲቲው ሁለት አንኳር የሪፎርም አጀንዳዎችን እየተገበረ መሆኑን ያነሱት ፕ/ር ፍቅሬ እንደ ምርምር ዩኒቨርሲቲ የምርምር ዩኒቨርሲቲ ሊያሟላቸው የሚገቡ መስፈርቶችን በብቃት ለማሟላት እና በቅርብ ዓመታት ውስጥም ራስ-ገዝ ዩኒቨርሲቲ መሆንላይ በማተኮር በርካታ ስራዎች የተሰሩ መሆናቸውን፤ ወደ የራስ-ገዝነት የሚደረገው ጎዞውም በአንድ ጊዜ የሚደረግ ሳይሆን በሥራ አመራር ቦርድ በሚሰጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በሶስት ምዕራፎች ማለትም በመጀመሪያ የአካዳሚያዊ ነጻነትን በማረጋገጥ፣ ቀጥሎም የሰው ሀብትን የማስተዳደር ነጻነት



አቶ ተፈሪ ጊሼ
የስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ሥራ አስፈጻሚ

እና በመጨረሻም የፋይናንስ ነጻነትን በማረጋገጥ የሚከናወን መሆኑን እና ከዚህ አኳያም በ2016 ልዩ ልዩ አመርቂ ስራዎች የተሰሩበት ዓመት መሆኑን ለካውንስሉ አብራርተዋል። እንደ ዩኒቨርሲቲ በአካዳሚክ ዘርፍ ፣በምርምርና ትብብር



ፕ/ር ፍቅሬ ደሳለኝ
የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚደንት

እንዲሁም በአስተዳደርና ልማት ረገድ በበጀት ዓመቱ የተሰሩ ሥራዎችና እንደተቋም በዓለም አቀፋዊነትና ትብብር ረገድ፣ በበጀት አጠቃቀምና ለሌሎች ጉዳዮች ላይ የሚቀርበውን ሪፖርት መሰረት በማድረግ የካውንስሉ አባላት በስፋትና በጥልቀት እንዲገመግሙ አሳስበዋል።

የበጀት ዓመቱ ዓመታዊ የመደበኛ እና የሪፎርም ስራዎች አፈጻጸም ሪፖርትም በአቶ ተፈሪ ጊሼ የስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ሥራ አስፈጻሚ አማካይነት የቀረበ ሲሆን በሪፖርቱም 2017 የትምህርት ዘመን ዩኒቨርስቲው የሚቀበላቸውን ተማሪዎች ለመወሰን በዩንቨርስቲው የመቀበያ መስፈርት መሰረት በፒኤች ዲ ፕሮግራም 647 እንዲሁም የማስተርስ ዲግሪ ፕሮግራም ደግሞ 6161 ተወዳዳሪዎች ተለይተው የመግቢያ ፈተና (GAT) እንዲፈተኑ ወደ ትምህርት ሚኒስቴር ስማቸው መተላለፉ እና ለ3024 ሰልጠኞች የአቅም ግንባታ ስልጠና መሰጠቱ በሪፖርቱ ተመላክቷል። በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ በመደበኛ 1477፣ በተከታታይ ትምህርት 768 እና በክረምት 23 ጠቅላላ ድምር 2268 (ወንድ 1762 ሴት 506) ተማሪዎች የአካዳሚክ መስፈርቱን በሟሟላታቸው በሰኔት ጸድቆላቸው መመረቅ መቻላቸው ከቀረበው ሪፖርቱ ለመረዳት ተችሏል፡ ፡ በ2016 የትምህርት ዘመን 21 መምህራን የከፍተኛ ዲፕሎማ ፕሮግራም (HDP) ተከታትለው ያጠናቀቁ ሲሆን ለ81 መምህራንም ከአሪዞና ስቴት ዩኒቨርስቲ ጋር በመተባበር የኦን ላይን ስልጠናን ለመስጠት ተችሏል።

የምርምር ስራዎችን በተመለከተም በ2015 የበጀት ዘመን የተከናወኑ 67 የምርምር ሥራዎች መካከል አሥራ አምስቱ (አምስት ከአገር ውጭ፤ አስር በአገር ውስጥ) በሣይንሣዊ የምርምር መጽሔቶች የታተሙ ሲሆን የተቀሩት 52 ምርምሮች በዩኒቨርሲቲው እና በውጭ ጆርናሎች በሚታተምበትን ሂደት ላይ ክትትልና ድጋፍ እየተደረገ ይገኛል። በተጨማሪም በዩኒቨርሲቲው ተመራማሪዎች የተሠሩ እና የታተሙ ተጨማሪ 213 የምርምር ሥራዎች ወደ መረጃ ቋት እንዲገቡ የተደረገ ሲሆን ከ2011 - 2015 በተካሔዱ ዓመታዊ የምርምር ጉባዔዎች ላይ የቀረቡ የጥናት ወረቀቶች መድብል (ፕሮሲዲንግስ) በዩኒቨርሲቲው ድረ ገጽ ላይ ለተደራሲያን ተደራሽ ሲደረጉ የዘጠነኛው ዙር አገር አቀፍ የምርምር ጉባዔ በታቀደው እና በተሳካ ሁኔታ ተካሂዷል። ከዚህ በተጨማሪም በርካታ የማማከር እና የማህበረሰብ አገልግሎቶች በበጀት ዓመቱ በዩኒቨርሲቲው የተሰሩ መሆናቸውን አቶ ተፈሪ በሪፖርታቸው አመላክተው ልዩ ልዩ ፖሊሲዎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች የተከለሱ እና የተቀረጹ መሆናቸውንም ገልጸዋል። የአጋርነትና ትስስርን ለማጠናከርም ከአገር ውስጥና አለም አቀፍ ተቋማት ጋር የጋራ ኘሮግራሞችን ለማካሄድ የተጀመሩ ነባር ግንኙነቶችን ለማጠናከርና አዳዲስ ግንኙነቶችንም ለመፍጠር በኮሌጆችና በትምህርት ክፍሎች የተለያዩ ስራዎች በመሰራት ላይ መሆናቸው በሪፖርቱ ተገልጿል። የበጀት፣ የፋይናንስ፣ የንብረት አስተዳዳር አገልግሎትን ውጤታማነትን ለማሻሻልና ለማረጋገጥ የተደረገውን ጥረትም አስመልክቶ አቶ ተፈሪ በሪፖርታቸው እንዳመለከቱት ዩኒቨርሲቲው በ 2016 ዓ.ም የተጣራ ገቢ ብር 51,067,302 .85 የውስጥ ገቢ ማስገባት መቻሉን ለካውንስሉ ገልጸው በአጠቃላይ በጀት አመቱ ለዩኒቨርሲቲው ዕቅድ ማስፈፀሚያ የሚውል ከመንግስትና ከውስጥ ገቢ ለመደበኛና ለካፒታል በጀት በድምሩ ብር 886,131,610.00 ዉስጥ ብር 870,131,800.30 ጥቅም ላይ የዋለ እና አጠቃላይ የበጀት አጠቃቀሙም 98.19% መሆኑን በሪፖርታቸው አመላክተዋል። በቀረበው ሪፖርት ላይም የካውንስሉ አባላት በስፋት የተወያዩ ሲሆን ዩኒቨርሲቲው ተልዕኮውን በላቀ ሁኔታ እንዲወጣ ለማስቻል መስተካከልና መሟላት የሚገባቸውን ግብዐቶችና አካሄዶችን በማንሳት ለወደፊቱ ጠንክሮ መስራት እንደሚገባቸው አመላክተዋል።

በተጨማሪም በ2017 የበጀት አመት በዩኒቨርስቲዉ ያሉ ዘርፎች የሚያተኩሩባቸዉ ቁልፍ እቅድ አመላካች ላይ በዶ/ር አብረሐም ሃጎስ የፕሬዚዳንት ጽ/ቤት ኃላፊ ማብራርያ ተሰጥቷል። በግምገማ መድረኩ ማጠቃለያ ላይም ፕ/ር ፍቅሬ በሰጡት ማጠቃለያ በአካዳሚክ ዘርፉ በ2017 ከትምህርት ሚኒሲቴር በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት በመጀመሪ ዲግሪ ዩኒቨርሲቲው ለሚቀበላቸው ተማሪዎች ከወዲሁ ኮሌጆችና የትምህርት ክፍሎች ሰፊ ስራ መሰራት እንዳለባቸዉ አሳስበዋል። ምርምርን በተመለከተም በተማሪዎች በሚሰሩ የምርምር ስራዎች ላይም የመምህራን ተሳትፎ



ማደግ እንደሚገባው አሳስበዋል። በአጠቃላይ ሲታይም በዩኒቨርሲቲው በበጀት ዓመቱ ሰፋፊ ስራዎች የተሰሩበት እና ስኬቶች የተመዘገቡበት ዓመት እንደነበር ገልጸዋል። ለዚህም መሳካት ድርሻቸዉን ለተወጡ ሰራተኞች እና አመራሮች ምስጋና በማቅረብ ማንኛዉም ተቋም የሚያድገዉም ሆነ የሚለወጠዉ በሰዉ ሀይሉ መሆኑን በመግለጽ ፤ የተቋም መለወጥ ማለት የሰራተኛ መለወጥ ጭምር እንደሆነ ለዚህም በ2017 የትምህርት ዘመን ሁሉም የተቋሙን ራዕይ በላቀ ደረጃ ለማስፈጸም ሀላፊነቱን እንዲወጣ አሳስበዋል።



# 33ኛው ሀገር አቀፍ የትምህርት ጉባኤ በኢሲሰዩ ተካሄደ

33ኛው ሀገር አቀፍ የትምህርት ጉባኤ “ፍትሃዊና ጥራት ያለው ትምህርት ለሁሉም” በሚል መሪ ሃሳብ የከፍተኛ ትምህርት ልማት ዘርፍ መድረክ በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ነሀሴ 23 ቀን 2016 ዓ.ም በህዳሴ አዳራሽ ተካሄደ።



ፐ/ር ፍቅሬ ደሳለኝ
የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚደንት



ክቡር አቶ ኮራ ጡሽኔ
የትምህርት ሚኒስትር ዴኤታ

በጉባኤው መክፈቻ ላይ ክቡር አቶ ኮራ ጡሽኔ የትምህርት ሚኒስትር ዴኤታ ባደረጉት ንግግር በከፍተኛ ትምህርት ዘርፉ ላይ ከፍተኛ መዋዕለ ነዋይ በማፍሰስ በተደረገው ጥረት መንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ተደራሽነት በማስፋት ረገድ ከፍተኛ ውጤት የተመዘገበ መሆኑንና የትምህርት ጥራትን ለማጎልበት በትኩረት እየሰራ እንደሚገኝ ተናግረዋል። ክቡር ሚኒስቴር ዴኤታው አያይዘውም ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ባሉባቸው አካባቢዎች የዜጎችን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ህይወት የሚያሻሽሉ ተግባራትን በማከናወን እንዲሁም በሀገራዊ የልማት መስኮች ተጠናክረው ማስቀጠል እንደሚገባቸውና ከመማር ማስተማርና የማህበረሰብ አቀፍ የምርምር አገልግሎት በተጨማሪ በማህበረሰቡ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ላይ በስፋት መስራት እንደሚገባቸው፣ የተቀረጹት የከፍተኛ ትምህርት የሪፎርም አጀንዳዎች ተግባራዊነት ጠንክረው መስራት እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ፐ/ር ፍቅሬ ደሳለኝ በበኩላቸው ባደረጉት የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ በሀገራችን ያለውን የሲቪል ሰርቫንቱን አቅም የመገንባት ልዩ ተልዕኮውን ይዞ ከተቋቋመበት ከ 1988 ዓ.ም ጀምሮ





Hotline: +251-116-46-30-15/Tel.0116462887/Fax:0116463016/P.O.Box5648/E-mail: IPRD@ecsu.edu.et or Pr.ecsu@gmail.com
Website: www.ecsu.edu.et FM Radio:-100.5MHz/ Facebook: Ethiopian Civil Service University



ላለፉት ዓመታት ለመንግስት ሠራተኞችንአቅምበመገንባት፣ የአመራሩንና የሰው ኃይል እጥረትን በመቅረፍ ረገድ ከፍተኛ ስራዎችን መስራት የቻለ እና ተልዕኮውንም በብቃት በመወጣት ላይ ያለ ተቋም መሆኑን በመግለጽ ዩኒቨርሲቲው ባስመረቃቸው ከ ሰባ ሺህ በላይ ሲቪል ሰርቫንቶች እንዲሁም ባፈራቸው ተጽዕኖ ፈጣሪ ሚኒስትሮች፣ ከንቲባዎችና ከፍተኛ ባለሙያዎች ለሀገር ሁለንተናዊ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከተ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ዩኒቨርሲቲው ሲመሰረት ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት እንደነበር እና ከዚያም በኋላ ለተለያዩ ሚኒስትር መስሪያ ቤቶች ተጠሪ እንደነበር የገለጹት ፕ/ር ፍቅሬ ከ 2014 ጀምሮ ለትምህትርት ሚኒስቴር ተጠሪ እንዲሆን የተደረገ በመሆኑ ትክክለኛ ቦታውን እንዲያገኝ የተደረገ መሆኑንም አስረድተዋል፡፡

ዩኒቨርሲቲው በሀገሪቱ ያለውን የፋይናንስ አሰራር እና የመንግስት ግዥ ሥርዓት መዘመን፣ ለዴሞክራሲ ሥርዓት መጎልበት፣ ለፍትሕና የዳኝነት አገልግሎት መሻሻል፣ ከተሞች በፕላን እንዲመሩ ለማስቻል በከተማ ልማት እና በሌሎችም ተዛማጅ መስኮች ስልጠናዎችን በመስጠት ትልቅ አስተዋጽኦ እያበረከተ መሆኑንም እንዲሁም በአሁኑ ወቅትም የተለያዩ ሀምሳ አራት የትምህርት ፕሮግራሞችን እየሰጠ ያለ ሲሆን ከእነዚህም መካከል 91% የድህረ ምረቃ ፕሮግራሞች መሆናቸውን በመግለጽ በቀጣይም የቅበላ አቅሙን በማሳደግ የበለጠ ተደራሽ ለማድረግና ጥራት ያለው ትምህርትን ለማህበረሰቡ ለመስጠት ይሰራል ብለዋል። በመንግስት በጀት ከሚሰሩ የጥናትና ምርምር ውጤቶች ባሻገርም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከፌዴራል፣ ክልሎችና ከተማ አስተዳደር ተቋማት እና በተለያዩ ሀገራት ከሚገኙ ዩኒቨርሲቲውች ጋር በመተባበር የተጀመሩ አጋርነቶችን በማጠናከር ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸው የምርምርና ማማከር አገልግሎት እየተሰጠ እንደሚገኝ ጠቅሰዋል። በጉባኤው ላይም የ2016 ዓ.ም ዕቅድ አፈፃጸምና የ2017 ዓ.ም ዕቅድ፣ የአካዳሚክ ጉዳዮች፣ የምርምርና የማኅበረሰብ ጉድኝት፣ የአይሲቲና ዲጂታል ትምህርት፣ የአስተዳደርና መሠረተ ልማት የሪፎርም ስራዎችን ፣ የቁልፍ አፈፃጸም አመላካች ጉዳዮች ላይ ሪፖረቶችና የተለያዩ ጽሑፎች የቀረቡሲሆንየፓናልውይይትና በቀረቡት ሪፖረቶችና ጽሑፎች ላይም ሰፊ ውይይት ተደረጓል፡፡

## በኢሲሰዩ የችግኝ ተከላ መርሐ- ግብር ተካሄደ

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ሰራተኞች ነሐሴ 17 ቀን 2016 ዓ.ም “በአንድ ጀምበር 600 ሚሊዮን ችግኞችን በመትከል ዓሻራችንን እናኑር፡፡” በሚለው መርሃ ግብር መሰረት በዩኒቨርሲቲው ቅጥር ጊቢ ውስጥ ችግኞችን በመትከል አሻራቸውን አኑረዋል፡፡



በአረንጓዴ አሻራ መርሐ-ግብሩ የዩኒቨርሲቲው ሰራተኞች እና ተማሪዎች ተሳትፈዋል ። በመርሐ-ግብሩ እያንዳንዱ ሰው ከ15 በላይ ችግኞችን የተከለ ሲሆን፤ ከተተከሉ ችግኞች መካከልም ለምግብነት የሚውሉና ለጥላነት የሚያገለግሉ እንደሚገኙበት የችግኝ ተከላው አስተባባሪ አቶ አንዷለም አቓምየለህ ገልጸዋል ።





# የኢሲሰዩ ያስገነባቸውን የንግድ ሱቆች ለተጠቃሚዎች አስተላለፈ

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ያስገነባቸውን 25 የንግድ ሱቆች በዩኒቨርሲቲው ለሚሰሩና በየካ ክፍለ ከተማ በወረዳ 09 ለሚገኙ በአነስተኛ ገቢ ለሚተዳደሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ጳጉሜ 1 ቀን 2016 ዓ.ም በዕጣ አስተላለፈ፡፡



በርክክብ ሥነ-ስርዓቱ ላይ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚደንት ፕሮፌሰር ፍቅሬ ደሳለኝ ለተጠቃሚዎች ባስተላለፉት መልዕክት ተጠቃሚዎቹ በተለይ አነስተኛ ገቢ ያላቸዉ ተጨማሪ ገቢ ማስገኛ እንደሚሆን በመግለጽ ዩኒቨርስቲዉ እንዲህ አይነት ድጋፍ ሲያደርግ ለሁለተኛ ግዜ መሆኑን በመግለጽ ወደፊትም በተቻለመጠንማህበራዊግዴታዉንእንደሚወጣገልጸዋል፡ ፡ የተዘጋጀው ውል በጥንቃቄ በመረዳት የተቀመጠውን ህግና ደንብ አክብረው፣ የሚጠበቅባቸውን ግዴታ በአግባቡ በመወጣት ፤ በተለያዩ ነገር ግን ገበያ ተኮር ባደረጉ የስራ መስኮች ላይ ተሰማርተው እንዲሰሩ አሳስበዋል፡፡ የዚህ ዕድል ተጠቃሚ ለመሆን በመቻላቸው እንኳን ደስ አላችሁ በማለት መልካም የሥራ ስኬትን ተመኝተዋል፡፡





ኢሲሰዩ ካስገነባቸው 25 ሱቆች መካከል 13 ለዩኒቨርሲቲው ዝቅተኛ ደመወዝ ለሚከፈላቸው ሰራተኞች የተሰጡ ሲሆን ቀሪዎቹ ደግሞ የየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 09 ለይቶ ላቀረባቸው አነስተኛ ገቢ ላላቸዉ የህብረተሰብ ክሎች ተሰጥተዋል፡፡ የሱቆቹን ቁልፎች የወረዳዉ ስራ አስፈጻሚ ከኢሲሰዩ ፕሬዚዳንት ተረክበዋል፡፡

# ECSU Signed MoU with School of Planning and Architecture

Ethiopian Civil Service University Signed a Memorandum of Understanding (MoU) with School of Planning and Architecture to conduct joint research on various thematic areas (Urban Planning and Architecture, Transport, Environment, Land Administration, Housing and Real Property Valuation, Infrastructure Planning, Urban Management) and the exchange of Architecture and Planning professors and scholars.



The MoU was signed by ECSU President, Professor Fikre Dessalegne and the Director of the School of Planning and Architecture, Prof. Dr. Virendra



Kumar Paul held at New Delhi. The MoU provided notable opportunities and comprehensive and strategic partnership to promote collaborative research, faculty interactions, and cultural engagement between the two institutions. It will also pave the way for academic exchanges, joint research initiatives, and collaborative projects that will enrich the educational experience at both institutions.

The partnership aimed to achieve the ECSU's intended goals and vision of becoming a Center of Excellence in Urban Development and Engineering.

The School of Planning and Architecture, (SPA New Delhi) is an Institution of National Importance imparting education in Architecture, Planning, and Design and provides training at various levels and offers academic programs in specialized fields at a Bachelor's, Master's and Doctoral level. SPA is ranked consistently among the top 5 schools in India.

Ethiopian Civil Service University
Committed to Excellence in the Public Sector

Contact Address:
Hot line: +251-116-46-30-15
Tel.0116 46 2887
Fax: 0116463016
P.O.Box5648
E-mail: IPRD@ecsu.edu.et
Pr.ecsu@gmail.com
Website: www.ecsu.edu.et
Tweeter: @ECSU tweets
FM Radio:-100.5MHz
Facebook: Ethiopian Civil Service University